# የእርምት ማስታወቂያ

## ለአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክስዮኖች በሙሉ

የአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ለማከናወን ሰኔ 15 ቀን 2017 ዓ.ም. በወጣው ማስታወቂያ ላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች መካከል በተራ ቁጥር 9 እና ተራ ቁጥር 10 ላይ የተመለከቱት መስፈርቶች ተፈፃሚነት የሌላቸው ወይንም የማያገለግሉ መሆኑን እየገለፅን በዚህ የማረሚያ ማስታወቂያ መሰረት ሰኔ 15 ቀን 2017 ዓ.ም. በወጣው ማስታወቂያ ላይ የተዘረዘሩትን ሌሎች መስፈርቶች መሰረት በማድረግ እስከ ማጠናቀቂያው እለት መስከረም 15 ቀን 2018ዓ.ም. ድረስ ጥቆማዎችን የምንቀበል መሆናችንን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

የአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ

# ማስታወቂያ

## ለአዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ. ባለአክስዮኖች በሙሉ

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ለማከናወን እንዲቻል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ መሠረት የኢንሹራንስ ኩባንያው የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ በኩባንያው የባለአክሲዮኖች 30ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መመረጡ ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት የተሰየመው የቦርድ አባላት የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ (Board Nomination and Election Committee) የዳይሬክተሮች ቦርድ ዕጩ አባላትን ጥቆማ ከ ሰኔ 15 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ መስከረም 15 ቀን 2018 ዓ.ም ብቻ የሚቀበል ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SIB/32/2012 እና SIB/48/2019 አንቀጽ 8 መሠረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች  የሚያሟሉ ዕጩ የቦርድ አባላትን እንድትጠቁሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

1. ዕድሜ  30 ዓመት እና በላይ የሆነ/ች እና የኩባንያው የዴይሪክተሮች ቦርድ ሆኖ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ/ች፣
2. የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ አባል ያልሆነ/ች፣ የኩባንያው ወይም የሌላ መድን ሰጪ ኩባንያ ሠራተኛ ያልሆነ/ች እና በሌላ የገንዘብ ተቋም የቦርድ አባል ያልሆነ/ች፣
3. የሥራ ልምድን በሚመለከት በንግድ ሥራ፣ በሕግ ሙያ አገልግሎት፣ በመድን ሥራ ወይም ተዛማጅ መስኮች በቂ የሥራ ልምድ ያለው/ላት፣

4. የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በዕጩነት ሊጠቆም ይችላል፤ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት ዕጩ ሲደረግ የህግ ሰውነት ያለውን ድርጅት በቦርድ ውስጥ የሚወክል አንድ የተፈጥሮ ሰው ዝርዝር መረጃ መገለፅ ይኖርበታል፤
5. በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ተግባር ያልፈጸመ/ች፣ ለገንዘብ ተቋማትና ለተቆጣጣሪ አካል ሐሰተኛ መረጃ ያልሰጠ/ች፣ የስነ-ምግባር ደንቦችን ባለማክበር የስነ-ስርዓት እርምጃ ያልተወሰደበት/ባት፣ በሙስና ወንጀል ተከሶ ያልተፈረደበት/ባት እና የመምረጥና የመመረጥ መብቱ/ቷ ያልተገደበ፣
6. የፋይናንሻል ጤናማነትን (Financial Soundness) መስፈርት የሚያሟላ፤ ማለትም በኪሳራ ላይ ያልሆነ/ች፣ የታክስና የባንክ ግዴታዎቹን የተወጣ/ች፣
7. ከ18 ዕጩዎች ውስጥ 1/3ኛው ማለትም ስድስት ዕጩዎች የሚጠቆሙት ከኢንሹራንስ ኩባንያው ጠቅላላ የተፈረመ ካፒታል 2% በታች ባላቸው ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክስዮኖች (Non-Influential Shareholders) ብቻ ሲሆን ቀሪዎቹ 12 ወይም 2/3ኛ ዕጩዎች በሁሉም ባለአክስዮኖች ከሚጠቆሙት ውስጥ ሆኖ የፆታ ተዋጽኦን ያማከለ መሆን ይኖርበታል፡፡

8. የትምህርት ደረጃ
   ሀ. ቢያንስ 75% የሚሆኑት የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ከታወቀ የትምህርት ተቋም ያላቸው፣
   ለ. የተቀሩት 25% ቢያንስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ያጠናቀቁ መሆን ይኖርባቸዋል ፡፡
9. አንድ የአገልግሎት ዘመን (ሦስት ዓመት) ያገለገሉ ዳይሬክተሮች በድጋሚ ሊጠቆሙ ይችላሉ፡፡ ከነባር የቦርድ አባላት ውስጥ ሁለት የአገልግሎት ዘመን ወይም ስድስት ዓመት ቢሞላቸውም፣ የዳይሬክተሮችን ልምድ ቀጣይነት ለማረጋገጥ በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከተመረጡ፣ ከጠቅላላ የቦርድ አባላት 1/3ኛው ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

**ማሳሰቢያ**

1. ጥቆማውን በአዋሽ ታወርስ አዋሽ ኢንሹራንስ ህንፃ 5ኛ ፎቅ በአካል በመቅረብ ወይም በመልዕክት ሳጥን ቁጥር 12637 አ.አ "ለአዋሽ ኢንሹራንስ የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ ጽ/ቤት" በመላክ ወይንም በፋክስ ቁጥር 011-557-02-46 ወይንም በኢሜይል አድራሻ aicbnc@awashinsurance.com ማቅረብ ይቻላል፡፡
2. የጥቆማ ማቅረቢያ ፎርሙን ከኩባንያው ዋና መ/ቤት የኮሚቴው ቢሮ ወይም በፋይናንሻል ማኔጅመንት የሥራ ዘርፍ ስር ካለው የባለአክሲዮኖች ክፍል ወይም ከኩባንያው ቅርንጫፎች ወይም ከኩባንያው ድረ-ገጽ (ዌብሳይት) **www.awashinsurance.com** ማግኘት ይቻላል፡፡

3. ተፅእኖ ፈጣሪ የሆኑ ባለአክሲዮኖች እስከ ስድስት እጩዎች መጠቆም የሚችሉ ሲሆን ተፅእኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ደግሞ እስከ ዘጠኝ እጩዎች መጠቆም ይችላሉ።
4. ለጥያቄና ተጨማሪ ማብራሪያ በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 0115 57 00 01 የውስጥ ቀጥር 252 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል።
5. ከመስከረም 15 ቀን 2018 ዓ.ም በኋላ የሚቀርቡ ጥቆማዎችም ሆኑ ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚደርሱ ጥቆማዎች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን ከወዲሁ በአክብሮት እናሳውቃለን።

***የዳይሬክተሮች ቦርድ የምልመላና አስመራጭ ኮሚቴ***

***አዋሽ ኢንሹራንስ አ.ማ.***

# እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ለመጠቆም የተዘጋጀ ቅጽ 1
# ተፅእኖ ፈጣሪ ለሆኑ ባለአክስዮኖች

- ተጽእኖ ፈጣሪ ባአክስዮን እስከ 6 ሰው መጠቆም ሲችሉ ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆነ/ኑ ባለአክስዮኖች እስከ 9 ሰው መጠቆም ይችላሉ።
- ጥቆማው የቀረበው በውክልና ከሆነ የህጋዊ ውክልና ሰነድ ኮፒ ተያይዞ መቅረብ አለበት።
- ተጠቃሚው ድርጅት ከሆነ የድርጅቱ ስም እና ድርድቱን የማወክል የተፈጥሮ ሰው ስም ይገለፅ።

| ተ.ቁ | የተጠቋሚ ባለአክስዮን ስም ከነአያት | ጾታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የተጠቋሚው ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | |
| 2. | | | | | |
| 3. | | | | | |
| 4. | | | | | |
| 5. | | | | | |
| 6. | | | | | |

የጠቋሚ ባለአክስዮን ስም ከነአያት ________________________________________

የአክስዮን ብዛት ______________________

ስልክ ቁጥር ________________________

ፊርማ ___________________________ ጠቋሚው ድርጅት ከሆነ ማህተም ይደረግበት

# እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ለመጠቆም የተዘጋጀ ቅጽ 2
# ተፅእኖ ፈጣሪ ላልሆኑ ባለአክስዮኖች

- ተጽእኖ ፈጣሪ ባአክስዮን እስከ 6 ሰው መጠቆም ሲችሉ ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆነ/ኑ ባለአክስዮኖች እስከ 9 ሰው መጠቆም ይችላሉ፡፡
- ጥቆማው የቀረበው በውክልና ከሆነ የህጋዊ ውክልና ሰነድ ኮፒ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
- ተጠቃሚው ድርጅት ከሆነ የድርጅቱ ስም እና ድርድቱን የሚወክል የተፈጥሮ ሰው ስም ይገለፅ፡፡

| ተ.ቁ | የተጠቋሚ ባለአክስዮን ስም ከነአያት | ጾታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | የተጠቋሚው ስልክ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | | | | | |
| 2. | | | | | |
| 3. | | | | | |
| 4. | | | | | |
| 5. | | | | | |
| 6. | | | | | |
| 7. | | | | | |
| 8. | | | | | |
| 9. | | | | | |

የጠቋሚ ባለአክስዮን ስም ከነአያት ______________________________________________

የአክስዮን ብዛት ______________________________

ስልክ ቁጥር __________________________________

ፊርማ _____________________________________ ጠቋሚው ድርጅት ከሆነ ማህተም ይደረግበት